# ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ

አንዳንድ ሰዎች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምንድን ነው ማርያም መግደላዊትን ገና ወደ አባቴ አላረግሁማና አትንኪኝ ብሎ ቶማስን ግን እንዲነካ የፈቀደለት በማለት ይጠይቃሉ። የተለያየ ማብራሪያም ለዚህ ጥቅስ ተሰጥቷል። ለመሆኑ በትክክለኛው የዚህ ጥቅስ መልእክቱ ምንድን ነው?

በመሠረቱ ይህ ጥቅስ የሚገኘው በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 20 ቁጥር 17 ላይ ነው፤ እንዲህም ይላል «ኢየሱስም። ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ። እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት። መግደለዊት ማርያም መጥታ ጌታን እንዳየች ይህንም እንዳላት ለደቀ መዛሙርቱ ነገረች። »

ዮሐንስ «ኢየሱስም ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ» ብሎ ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህ አጻጻፉ የሚመስለው መግደላዊት ማርያም ክርስቶስ ከተነሳ በኋላ እንዳትነካው የከለከላት ነው፤ ይሁን እንጂ ዮሐንስ ማመልከት የፈለገው ማርያም መግደላዊት በልቧ ያሰበችውን አውቆ ቅድሚያ ልታደርግ የሚገባውን ነገራት እንጂ በቀጥታ እንደተጻፈው መተርጎም የለበትም። ምክኒያቱም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 28፤9 ላይ ሴቶቹ (መግደላዊትና ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም) እንደነኩት በግልጽ እንዲህ ይላል፣ እነሆም ፥ ኢየሱስ አገኛቸውና። ደስ ይበላችሁ አላቸው። <u>እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት።</u> በዚያን ጊዜ ኢየሱስ አትፍሩ ፤ ሄዳችሁ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ተናገሩ ፥ በዚያም ያዩኛል አላቸው።

ስለዚህ የዮሐንስ አባባል ...«ከሞት መነሳቴንና የማነጋግርሽ እኔ እንደሆንኩ አምነሻል አሁንም ገና ስላላረግሁም እዚህ ምድር ላይ እቆያለሁም ላንቺም በቂ ጊዜ አለ፤ ይልቅ ቶሎ አሁኑኑ ሂጂና ለወንድሞቼ ከሞት መነሳቴን ንገሪያቸው ለማለት ነው እንጂ ዐረፍተ ነገሩ ከተነሳሁ በኋላ ሴት አትነካኝም ለማለት አይደለም። በሁሉም ወንጌሎች ላይ ትንሣኤውን አስቀድሞ ያየችው ማርያም መግደላዊት እንደሆነች ተጽፏል። ሴቶች ለመንካት በቂ ባይሆኑ ኖሮ አስቀድሞውኑ ከሐዋርያቱ ለአንዳቸው በተገለጸ ነበር። ስለዚህ ትንሣኤውን ከማንም በፊት ለማየት ለታደሉ፤ መንካት አልተፈቀደላቸውም ቢባል አያስኬድም። እንዲያውም ማርያም መግደላዊት የትንሣኤውን ዜና ሄዳ ለሐዋርያት በማብሰሯ፤ ሐዋርያ ለሐዋርያት ተብላለች።

በአንጻሩ ደግሞ ክርስቶስ ለምንድን ቶማስ እንዲነካው ፈቀደለት ለሚለው፤ በተነሳ ቀን ምሽት ላይ አስቀድሞ ለሌሎቹ በተገለጠ ጊዜ ቶማስ አብሯቸው አልነበረም። በዚሁ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 20ቁጥር 25 ላይ እንዲህ ይላል«ሌሎችም ደቀ መዛሙርቱ ጌታን አይተነዋል ብለው ለቶማስ ሲነግሩት፤ እርሱ ግን የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ፣ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም አላቸው።»

በተነሳም በስምንተኛው ቀን ሁሉም ሐዋርያት ቶማስንም ጨምሮ ተሰብስበው በዝግ ቤት ውስጥ ሳሉ በመሀከላቸው ተገልጾ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ከጌታችን ከእርሱ ምንም የተሰወረ ነገር ስለሌለ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቶማስ ያለውን ስለሚያውቅ በመሀከላቸው ተገልጾ ሰላም ለእናንተ ይሁን ካለ በኋላ፤ ቶማስን ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው ፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን ያለው። (ዮሐ. 20፤25)

እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ቶማስ ይንካው አይንካው ግልጽ አድርጎ ይህ ዐረፍተ ነገር አያሳይ
ም ነገር ግን ክርስቶስ ክርስቶስ በእርግጥ የተነሳው እሱ መሆኑን ቶማስ እንዲያምን፤ እንዲዳብሰ
ው በፈቀደለት ጊዜ ቶማስ ማመኑን «ጌታዬ አምላኬ» ብሎ መናገሩም ነው።ጌታም ስላየኸኝ አም
ነሃል አለው እንጂ ስለነካኸኝ አላለውም።

ስለዚህ በዮሐንስ ወንጌል ላይ የተጻፈውን አባባል መረዳት ያለብን ክርስቶስ እነዚያ ደቀመዛሙር
ት በሙሉ ልብ አምነውት እንዲከተሉት እንደሚፈልግ፤ እንዲሁም እኛንም እነዚያ ሐዋርያቱ ያዩ
ትን ያላየነውን ደግሞ እንድናምን ፤ እምነተ ቢስ ሆነን እንዳንቀር ነው እንጂ፤ ክርስቶስን ከተነሳ
በኋላ ለመንካት የተፈቀደላቸው ሐዋርያቱ (ወንዶች) ብቻ ናቸው ለማለት አይደለም።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን።

በእደ ማርያም እጅጉ ረታ

ግንቦት 2001